# ግንቦት 7 በአማራው ላይ ለምን ደካሞችን መረጠ? (ጌታቸው ሺፈራው)

August 23, 2018

አርበኞች ግንቦት 7 ማንነትን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶች ጋር ሰርቷል። ለአብነት ያህል ኦነግ የራሱን ባንዲራ ዘርግቶ ከግንቦት 7 ጋር ተደራድሯል። ከትግራይ ትህዴን፣ እና ከሌሎቹም በማንነት የተደራጁ ነፃ አውጭና ተገንጣይ ቡድኖች ጋር ሰርቷል። ግንቦት 7 እነዚህን ድርጅቶች ለማለዘብ ሲጥር እንደነበር ተነግሯል። በቅርቡ በሰጠው መግለጫ ደግሞ ትህነግ/ህወሓት ውስጥም የለውጥ ሀይሎች እንዳሉና ከእነዚህ የለውጥ ሀይሎች ናቸው ካላቸው የትህነግ/ህወሓት አካላት ጋር እንደሚሰራ ገልፆአል።
አርበኞች ግንቦት 7 ከእነ ድክመቱ በአንድነት ጎራው ጠንካራ ከሚባሉት የመጀመርያው ምን አልባትም ብቸኛው ድርጅት ነው። ይህ ድርጅት የብሔር ድርጅቶችን ለማለሳለስና ለማሰባሰብ ሲጥር እንዲቆየም ተነግሯል። እስካሁን አሉ ከተባሉ የብሔር ድርጅቶች ጋር ተቀራርቦ ለመነጋገር ጥሯል፣ ወይንም ፍላጎት አሳይቷል። አንዳንዶቹን የእሱ ሜዳና መርህ ድረስ ሄዶ ተደራድሯቸዋል። አርበኞች ግንቦት 7 የኢትዮጵያ፣ ኦነግ የኦሮሚያ ሐገር ተወካይ እስኪመስል ድረስ ታግሶ ተደራድረዋል።

የአርበኞች ግንቦት 7 ከብሄር ድርጅት ጋር ግንኙነት የተለየ ሆኖ የምናገኘው በአማራው ላይ ብቻ ነው። በቅርቡ ስለ ትህነግ/ህወሓት የለውጥ ሀይል አካል መሆን መግለጫ በሰጠበት ወቅት እንኳ አብን ተመስርቶ ፈጣን እንቅስቃሴ እያደረገ ነበር። እንዲያውም በአርበኞች ግንቦት 7 አካባቢ ስለ አብን ያለው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን መገንዘብ እየተቻለ ነው። በአሁኑ ወቅት የአብንን ያህል ፈጣን እንቅስቃሴ እያደረገ ያለ በማንነት የተመሰረተ ድርጅት የለም። በአማራው ላይ ያለው እንቅስቃሴ የሰፋ ሆኖ እያለ አርበኞች ግንቦት 7 ከአማራው ጋር ለመስራት የመረጧቸው ሌሎች ግልፅ አላማ የሌላቸው ድርጅቶችን ነው።

ለአብነት ያህል ከ3 ሳምንት በፊት "ልሳነ ግፉአን" የተባለ ድርጅት ልኡካን ነን ያሉ አካላት ወደ አማራ ክልል መጥተው ነበር። የግለሰቦቹ የኋላ ማንነት ሲገለጥ በጥቅሉ ከግንቦት 7 ጋር መልካም ግንኙነት ያላቸው፣ አንዳንዶቹ ከግንቦት 7 እና ከጎንደር ሕብረት ጋር አብረው የሚሰሩ ሆነው ተገኝተዋል። የ"ልሳነ ግፉአን" ወኪሎች በአማራው ተጋድሎ ቁልፍ ሚና ያላቸውን እውቅ ሰዎች ለማግኘት ጥረት ያደረጉ ሲሆን በማንነት ሳይሆን ከአንድነት ሀይሉ ጋር የመስራት እቅድ እንዳላቸው ይፋ አድርገው ከሰዎቹ ጋር ሳይግባቡ ተመልሰዋል። እነዚህ ልዑካን ከመጡ ከቀናት በኋላ በአማራ ተጋድሎ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ሰዎች በቀጥታም የአርበኞች ግንቦት 7 ጋር እንዲሰሩ ጥያቄ የቀረበላቸው እንዳሉም ለማወቅ ተችሏል።

ይህኛው አልሳካ ሲልም በስም ተራዕዶ ስራ እንደሚሰራ የተገለፀው ጎንደር ሕብረት የአርበኞች ግንቦት 7 መንገድ ጠራጊ ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል። ከጎንደር ሕብረት መንገድ ጠራጊ የሆነው ልሳነ ግፉአን ሲሆን ከተመለሰ በኋላም የሚዲያ ሽፋን ያገኘበት አጋጣሚ ታይቷል። ጎንደር ሕብረት በጎ ስም ስለሌለው ስሙ በክፉ ያልተነሳው ልሳነ ግፉአን ቀድሞ መጥቷል።

ጎንደር ሕብረት የሲቪክ ማህበር ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ግን እንደሲቪክ ማህበር አልገባም። ጎንደር ሕብረትን የተቀበሉት ከአርበኞች ግንቦት 7 ጋር እየሰሩ ያሉት እነ የሸዋስ አሰፋ ናቸው። የጎንደር ሕብረት ነኝ ያለው ድርጅት እውቅ ፖለቲከኞችን ሰብስቦ አግንቷል። ወደ ባህርዳር በመምጣት እነ ገዱ አንዳርጋቸው ጋር ተወያይቷል። ከዛ በኋላ ነው ቆሜለታለሁ ወዳለው ጎንደር ያቀናው። በዚህ ወቅትም እንደ ፖለቲካ ድርጅት ቅስቀሳ በማድረግ፣ ጎንደር ጎሃ ሆቴል "በአማራነት መደራጀት መውረድ ነው" ሲል ተቃውሞ ስለገጠመው፣ ደብረታቦር ላይ መዝሙር ቀይሮ "አማራ" እያለ ቀስቅሷል።

ጎንደር ሕብረት ሲያደርጋቸው ከነበሩት እንቅስቃሴዎች መረዳት የሚቻለው የአርበኞች ግንቦት 7 መንገድ ጠራጊ ሆኖ እንደመጣ ነው። በጎንደር ሕብረት ላይ ለተነሱ ትችቶችን ወገባቸውን አስረው ሲከላከሉ የነበሩት የአርበኞች ግንቦት 7 አባላትና ደጋፊዎች ናቸው።

**የግንቦት 7 እና የትህነግ/ህወሓት መንገድ**

ትህነግ/ህወሓት ወደ ስልጣን ሲመጣ በማንነት የተደራጀ የአማራ ወኪል አልነበረም። የእነ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ጠንካራ ድርጅት ሲመሰረት ግን በአማራው ላይ የሚጋልበው ብአዴን የሚባል ደካማና መጠቀሚያ ድርጅት ፈጥሯል። ትህነግ/ህወሓት ስለ አማራው ቀና አመለካከት ቢኖረው ኑሮ ከብአዴን ይልቅ ከመአህድ ጋር መስራት ይችል ነበር። ያደረገው ግን የአማራው ጠንካራ ወኪል የሆነውን መአህድን በማጥላላት፣ በማጥፋት ብአዴን የሚባል ደካማና ስለ አማራ ሕዝብ የጠራና ይህ ነው የሚባል አላማ የሌለውን ፈረስ መጋለብ ነበር።

ትህነግ/ህወሓት ብአዴንን ያመጣው ኢህዴን ከተባለ አማራን ገዥ አድርጎ ከሚቆጥርና ጥላቻ የነበረበት ሕብረ ብሄራዊ ድርጅት ነው። በአሁኑ ወቅት አርበኞች ግንቦት 7 ከየትኛውም በማንነት የተደራጀ ሀይል ጋር ሲሰራና ለመስራት ፍላጎት እንዳለው ሲገልፅ በአማራው ላይ ግን መንገድ ጠራጊ ያደረጋቸው ግልፅ አላማ የሌላቸው ድርጅቶች ነው። ጠንካራ ሕዝባዊ መሰረት ያለውን አብን ጋር ምንም አይነት ፍላጎት ያለው አይመስልም።

ትህነግ/ህወሓት ብአዴን የሚባል ድርጅትን መጠቀሚያ ሲያደርግ ድርጅቱ ውስጥ አማራን የሚጠሉ አመራሮች ስለነበሩ ነው። ከግንቦት 7 ጋር እየሰሩ የሚገኙት እነ ጎንደር ሕብረትም አማራው በማንነቱ እንዲደራጅ አለመፈለጋቸው ብቻ ሳይሆን ቀናኢነት የሌላቸው፣ በስሙ የነገዱበት ናቸው። የትህነግ/ህወሓትን ያህል ነው ባይባልም አርበኞች ግንቦት 7 ለአማራው ቀና አመለካከት የለውም ተብሎ (ሕጋዊ ሰነዶቹ ተጠቅሰው) እየተወቀሰ ነው። ትህነግ/ህወሓት ውስጥ የለውጥ ሀይል ስላለ አብረን እንሰራለን እያለ፣ የትህነግ ተቃዋሚ ከሆነው ትህዴን ጋር እየሰራ፣ ከኦህዴድም ከኦነግም ጋር እየሰራ በአማራው ላይ ግን እንደመንገድ ጠራጊ እያያቸው ያሉት እነ ጎንደር ሕብረትን ነው። ከብአዴን ጋር ግንኙነት ሊኖረው እንደሚችል የእነ ገዱን ቡድን ላይ ባለው ቀና አመለካከት መገመት ቢቻልም አሁንም ለገዥዎቹ ከፈረስነት የተለየ አላማ የሌለው ብአዴን ይልቅ በተቃዋሚው ወገን ግን ከትህነግ/ህወሓት የመንገድ ጠራጊ የተለየ ስልት እየተጠቀመ እንዳልሆነ እየታየ ነው።

ኦሮሚያ ላይ ከገዥዎም ከተቃዋሚዎችም ጋር ሲሰራ፣ ከገዳዮቹ ከትህነግ ሰዎች መካከል የለውጥ ሀይል እንዳለ ጠቅሶ እንደሚሰራ ሲገልፅ በአማራው ላይ ስለምን ደካሞችን መረጠ? አርበኞች ግንቦት 7 ትህነግ እንዳደረገው በአማራው ላይ የሚፈልገው አጋር ነው ተላላኪ? ሕዝብን እየመዘበረ፣ እየሰደበ የሚያስገዛ ደካማ ወኪል ነኝ ባይ? በሕዝብ ላይ የሚጋለብ ፈረስ?

አርበኞች ግንቦት 7 ትህነግ/ህወሓት ወደአማራው በመጣበት መንገድ እየገሰገሰ ይሆን?

(ይቀጥላል)